# ፊንፊን አበዙ

እራሱን ዝቅ አርጎ ፣ አምኖ የተቀበለ
በራስ ለመመካት ፣ ጭራሽ ያልታደለ
ብዙ ፀጋ እያለው ፣ ሞልቶለት እያለ
ቅና ብሎ ፈጥሮት ፣ እየተቃጠለ
ትንሹን ትልቁን ፣ እየወነጀለ
        የሚታየው ለሱ ፣ ሁሌ እንደጎደለ
        በሌሎች ተገፍቶ ፣ እንደተበደለ ።

ፊደልን ቢቆጥር ፣ ቢማርም ጠንቅቆ
ዝቅተኛ ስሜት ፣ ሆኖበት ሽምቀቆ
በተጣባው ህመም ፣ የማያይ አርቆ
ከጎጥ ውቅያኖስ ፣ አይወጣ ተደፍቆ
ማር እንኳን ቢያልሱት ፣ ለሱ ግን እንቆቆ
        አርቆ እማያስብ ፣ ከጎጆው አዝልቆ
        ለመኖር የማይችል ፣ ከራሱ ጋር ታርቆ ።

ከከሰል ማርገቢያ ፣ በማይሻል ዲግሪ
ሳያውቅ አንዳዋቂ ፣ ታሪክን መስካሪ
የግዕዝ ደመኛ ፣ የቁቤ ተማሪ
ከራሱ የተጣላ ፣ እንኳን ከፈጣሪ
        ለአረብ የሚሰግድ ፣ ፈረንጅን አፍቃሪ
        ሰላምን የማያውቅ ፣ ሁሌም እሳት ጫሪ ።

ህዝብ ሳይወክለው ፣ እየተወከለ
የበቀል ጥላቻ ፣ መርዝ እየተከለ
በትዕቢት ተነፍቶ ፣ ስለተቆለለ
ሰላም አይገኝም ፣ የተደላደለ
        ለሚሰራው እውቀት ፣ ብስለት ካልታከለ
        እዚያ ቤት ያለ እሳት ፣ እዚህም ቤት አለ ።

ሌላው አቅም አልባ ፣ እሱ ብቻ ብርቱ
ያየውን የሚመኝ ፣ የማይሞላ ቋቱ
ድርድር አያውቁ ፣ ተሟግተው አይረቱ
እሱን ካልመሰለ ፣ ሰው ሁሉ ጠላቱ
እኔ ፣ እኔ ፣ ብቻ ፣ መኮፈስ በከንቱ
        ድፍን ያለ ፣ ጭፍን ፣ የተማረ ገልቱ
        ሌላው ሰው ደካማ ፣ እሱ ብቻ ብርቱ ።

በዋልጌዎች ተረት ፣ ክፉኛ የጦዙ
ነገን ተመልክተው ፣ አደብ የማይገዙ
የፀብ የጥላቻ ፣ ካርድ እየመዘዙ
ምን እንደሚያስከትል ፣ ዘረኝነት መርዙ
ህሊና የላቸው ፣ በርጋታ አይጓዙ
ምናል ሰከን ቢሉ ፣ አደብን ቢገዙ
        እነ ፊንፊኔዎች ፣ ፊንፊን አበዙ
        በምኞት መሳከር ፣ ምኑንም ሳይዙ ።

ታዛቢው

February 24, 2019